# መቅድም

ማኅበረ ቅዱሳን ይህን በብዙ ልፋትና ድካም ለኅትመት የበቃውን፣ ፰ኛውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት (ኢ.ቤ.ጥ.መ.) ለአንባብያን ሲያቀርብ በታላቅ ደስታ ነው፡፡ መጽሔቱ የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ሊያሳዩ የሚችሉ አምስት መጣጥፎችንና አንድ የመጽሐፍ ግምገማን ያካተተ ነው፡፡ ይህም በዘርፉ ያለውን መልከ ብዙ እውቀት በጨረፍታም ቢሆን ለማየት የሚያስችለንን ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡

መጽሔቱ ስድስት የምርምር ውጤቶችን የያዘ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ሦስቱ በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ሦስት የምርምር ውጤቶች ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ከቀረቡት መካከል የመጀመሪያው መጣጥፍ፣ በኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ከጥንት ጀምሮ እየተተገበረ በኖረው፣ በብራና ጥበብ አሠራርና አዘገጃጀት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የእስቴ ወረዳን በማሳያነት የተጠቀመው ይህ ጥናት፣ የብራና ጥበብ አሠራርና አዘገጃጀትን የሚያቀርብ ብቻ ሳይሆን፣ የሙያውን ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እንዲሁም ታሪካዊ ገጽታ የሚያሳይ ነው፡፡

ሁለተኛው መጣጥፍ፣ የፎክሎር ጥናት የቤተ ክርስቲያንን ገዳማትና ቅዱሳት ቦታዎች በማስተዋወቅ ረገድ የሚጫወተውን አዎንታዊና ገንቢ ሚና በማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ አተኩረው የተሠሩ ቀደምት የፎክሎር ጥናቶችን በመገምገም ባህላዊ ሁነቶችን፣ ንዋያተ ቅድሳትን፣ ገዳማትንና ቅዱሳት ቦታዎችን በጥልቀትና በስፋት ለመረዳት የፎክሎር ጥናቶች ጠቃሚ መሆናቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ያቀረበ ነው፡፡ በዚህ ቅጽ ሥር የተካተተው ሦስተኛው መጣጥፍ ደግሞ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ፋይዳ ያላቸውን ሚኒራሎች ሳይንሳዊ በሆኑ ስሌቶችና ስልቶች ለመተንተን የቻለ ነው፡፡ እነዚህ ሚኒራሎች በዋናነት በቤተ መዘክርና ቤተ መዛግብት ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፣ አብዛኛዎቹ በቤተ ክርስቲያኗ ባለቤትነት ሥር ያሉ ናቸው፡፡

አራተኛውና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከቀረቡት መካከል የመጀመሪያ የሆነው መጣጥፍ፣ የኢትዮጵያ ቤተ እምነቶች ካውንስል ከግጭት በኋላ የሚኖረውን ሚና የሚመረምር ነው፡፡ ጥናቱ በተለያዩ ቤተ እምነቶች ውስጥ ያሉ አማኞች ተከባብረው እንዲኖሩ ሃይማኖታዊ

ተቋማት ያላቸውን ወደር-የለሽ ድርሻ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ የድጓ መጽሐፍን መነሻ አድርጎ የቀረበው አምስተኛው መጣጥፍ በቅዱስ ያሬድ ጽሑፎች ውስጥ የሚታየውን ስለ ቅድስት ሥላሴ የነገረ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮን (Trinitarian Concept of Ecclesiology) የሚያሳይ ነው፡፡ መጣጥፉ ድጓን፣ መጽሐፍ ቅዱስንና ሃይማኖተ አበውን እንደ ማስረጃ በመጥቀስ የቤተ ክርስቲያኗ ዶግማዊ አስተምህሮ የሚመረምር ነው፡፡

ቅጹ ከእነዚህ አምስት መጣጥፎች በተጨማሪ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የተጻፈውንና Sodomites and the Wage of Sin በሚል ርእስ የቀረበውን መጽሐፍ የዳሰሰ ግምገማም አካቷል፡፡ ይህ ግምገማ በመጻሕፍት ላይ አተኩረው ትንተና በማድረግ ከቀረቡ ቀዳሚ የመጻሕፍት ግምገማዎች በተለየ መልኩ ትኩረቱን ያደረገው ጸሓፊውን ቃለ መጠይቅ በማድረግ አነሳሽ ምክንያታቸውንና ሐሳባቸውን ለመረዳት በመሞከር ላይ ነው፡፡ ገምጋሚው የተከተሉት ስልት መጽሐፉን ምዕራፍ በምዕራፍ በመዳሰስ የመጽሐፉን አጠቃላይ ጠንካራና ደካማ ጎን ለአንባቢ ማሳየት ነው፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ከሁሉ በፊት የእነዚህን ጥናታዊ ጽሑፎች ባለቤቶች፣ ገምጋሚዎች፣ ተባባሪ አርታዒዎችና የአርትዖት ኮሚቴ አባላት እንዲሁም በዚህ የኅትመት ሂደት ውስጥ የተሳተፉ አገልጋዮችና ባለሙያዎች በሙሉ ይህ ቅጽ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስና ፍሬ እንዲያፈራ ላደረጉት ያላሰለሰ ጥረትና እገዛ ምስጋናውን ይገልጻል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔትን ወደፊት የምናሳድገውና ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ የምንችለው በሁላችን የጋራ ጥረትና ትብብር ነውና እገዛችሁ ወደፊትም አይለየን ይላል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ይህ ቅጽ ለተመራማሪዎች፣ ለምሁራን፣ ለተማሪዎችና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚነሡ ጉዳዮችን ለማወቅ ጉጉት ላላቸው ግለሰቦች ጠቃሚ የመረጃ ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግል ተስፋ ያደርጋል፡፡

በመጨረሻም፣ ይህንን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለቤተ ክርስቲያናችን አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞችና እኅቶች እንዲሁም ለተመራማሪዎች፣ በልዩ ልዩ ዘርፍ ለተሠማራችሁ መምህራንና ተማሪዎች፣ በቀጣይ ለምናሳትመው ኢ.ቤ.ጥ.መ. ቁ.፱ ጥናታዊ ጽሑፎችን በመላክ የበኩላችሁን ምሁራዊና ክርስቲያናዊ አስተዋጽኦ እንድታደርጉ በማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ማእከል ስም ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ!**

**ደርብ አዶ (ፒ.ኤች.ዲ.)**

**የመጽሔቱ ዋና አርታዒ**

## Preface

The eighth issue of the Journal of Ethiopian Church Studies is now available for readers, and Mahibere Kidusan is excited to present it to its esteemed readers. This issue features a diverse range of scholarly works, including five articles and a book review that delve into various aspects of Ethiopian Church Studies. The contributions in this issue cover a wide array of topics related to Ethiopian church studies, offering valuable insights and perspectives that contribute to the rich tapestry of knowledge in this field.

Among the three articles in Amharic, the first one focuses on the process of parchment making in EOTC tradition by taking a case study of Este Woreda. The article does not only present the processes of parchment making but also shows the cultural, historical, and religious dimensions of it. The second article is concerned with the role of folklore in promoting monasteries and holy places in the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church. This study reviews previous folklore studies that focused on different aspects of the Ethiopian Orthodox Tewahedo church and presents evidence of how folklore studies help in better understanding the rituals, attires, sacred objects and histories of monasteries as well as other holy places. The third article in Amharic is a novel presentation of the science of analyzing minerals that are of religious and historical significance. These minerals are mainly found in museums and archives, and most of them are owned and/or contributed by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.

The fourth article, which is written in English, presents the role of the Inter-Religious Council of Ethiopia in a post-conflict setting. The article introduces the immense role of religious organizations in promoting peaceful coexistence of the believers of different religions. The fifth article presents Trinitarian Concept of Ecclesiology in the Writings of St. Yared by taking the Book of Dïgg$^{w}$a as

evidence. The article delves into the dogmatic concept as understood by the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church and as supported by evidence from the Book of Dïggʷa, the Holy Bible and Church Fathers.

This issue also adds a book review of Sodomites and the Wage of Sin, which is written by his eminence Abune Samu'el. Unlike previous book reviews that focused on the analysis of the book by the reviewers, this book review tries to understand the rationale and intention of the author by interviewing His Eminence Abunä Samu'el. The review presents a chapter-by-chapter analysis and overall assessment of the strengths and weaknesses of the book.

Mahibere Kidusan is grateful to the authors, reviewers, and editorial team for their dedication and hard work in bringing this volume to fruition. We are also indebted to everyone who has been involved in the process of publication and made this volume a reality. It is through our collective efforts that we can continue our mission of advancing scholarship in Ethiopian Church Studies. Mahibere Kidusan hopes that this issue will serve as a valuable resource for researchers, scholars, and enthusiasts alike, and we look forward to the continued growth and success of the Journal of Ethiopian Church Studies.

I would like to exploit this unique opportunity on the behalf of Mahbere Kidusan Research Centre to invite church fathers, scholars, researchers and students to contribute their manuscripts to our next issue of JECS No. 9.

Thank You!

Derb Ado, PhD

Editor-in-Chief